# ሌባ ላመሉ...

**ከተስፋዬ አሸናፊ**

Tigrai Online Feb. 06, 2014

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ባሳለፍነው ወር ጉባዔ አካሂዶ የተለያዩ ውሳኔዎችን አስተላልፏል፡፡ ከክልሉ ቴሌቪዥን እንደሰማነው የእፀዋትና ኳረንቲን ህግን ማፅደቅ፣ የአማራ ብዙሃን መገናኛ ሪፖርትን ማድመጥ፣ አዲስ ርዕሰ መስተዳድር መሰየም፤ የተጓደሉ የቢሮ ሃላፊዎችን ሹመት ማፅደቅና ከከፍተኛ እስከ ወረዳ ፍርድ ቤቶች የተጓደሉ ዳኞችን ማሟላት የጉባዔው አጀንዳዎች ነበሩ፡፡

ከነዚህ አጀንዳዎችና የም/ቤቱ ውሳኔዎች መካከል በተለይም በማህበራዊ ድረ ገፆችና በህትመት ውጤቶች ሲያወያየን የከረመው ም/ቤቱ ያከናወነው የርዕሰ መስተዳድር መተካካትን የተመለከተው አጀንዳ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ ኪራይ ሰብሳቢውና ፅንፈኛው የተቃዋሚ ሃይል እንደተለመደው ለርካሽ ፕሮፓጋንዳው ሊጠቀምበት ሞክሯል፡፡

ለፓርቲው አመራሮች ከኢሕአዴግ መርሆችና ህዝባዊ ባህሪዎች የተለየ የግል የፖለቲካ ስብዕና በማላበስ በፓርቲው አመራሮች መካከል የተፈጠረ ግጭት ውጤት እንደሆነ ለማስመሰል ተጥሯል፡፡ ይህንንም ጉባዔው አስቸኳይ በሚል ከመጠራቱ ጋር ለማያያዝና ከጀርባው አንዳች ተንኮል ያዘለ ያልተለመደ ክስተት ለማስመሰል ደፋ ቀና ተብሏል፡፡ አሁን በተጨባጭ የምንየውና የምንሰማው  ግን እውነታው ከነዚህ አሉባልታዎች የተለየ መሆኑን ነው፡፡

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ የኢሕአዴግ የመተካካት ስልት የግንባሩን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መስመር ቀጣይነት ማረጋገጥን አላማው ያደረገ መሆኑንን በተደጋጋሚ ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡ በአዲስ ራዕይ የንድፈ ሃሳብ መፅሄት የሐምሌ-ነሐሴ 2001 እትም ላይ እንደተቀመጠውም ፓርቲው ይህንን ጉዳይ የሚያየው የመስመሩን ቀጣይነት ከማረጋገጥ አኳያ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ ***"መስመሩን ለማስቀጠል አስፈላጊ ከሆነ እንኳንስ ከስልጣን መልቀቅ ህይወትን አሳልፎ መስጠት ተገቢ እንደሆነ በጥብቅ ያምንበታል ብቻ ሳይሆን በተግባርም ሲፈፅመው ኖሯል፡፡"*** በሚል አገላለፅም  መስመሩና መተካካቱ ያላቸውን ትስስር አስምሮበታል መፅሄቱ፡፡

በቅርብ አመታት ውስጥ እንደምናየውም ብአዴን ክልሉን እያስተዳደረ ባለበት ወቅት ለረጅም ጊዜ በሃላፊነት ያገለገሉትን አመራሮች የፊት ለፊት ረድፍ ተሰላፊነታቸውን እየለቀቁ አዳዲሶቹ ሃይሎች ቦታውን ተረክበው የሚሰሩበትን ሁኔታም ፈጥሯል፡፡ ይሄ የመተካካት ስርዓት ታዲያ አንዴ ተጀምሮ የሆነ ቦታ ላይ የሚቆም እንዳልሆነ ለመገመት ጠቢብ መሆንን አያሻም፡፡ አሁን በክልሉ የተካሄደው መተካካት በራሱ ይህን ያረጋግጣል፡፡

ብአዴን ክልሉን ማስተዳደር ከጀመረበት ከ1985 ጀምሮ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሃላፊነት፣ በምክትል ርዕሰ መስተዳድርነት፤ በአፈ ጉባዔነትና ያለፉትን ስምንት ተኩል አመታት ደግሞ በርዕሰ መስተዳድርነትና በድርጅቱ ስራ አስፈፃሚነት በድምሩ ለ21 አመታት ያገለገሉትን አቶ አያሌው ጎበዜን በአቶ ገዱ አንዳርጋቸው ባለፈው ወር ተክቷል፡፡ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው በክልሉ የተለያዩ የድርጅትና የመንግስት የስራ ሃላፊነቶች ተመድበው የሰሩ ሲሆኑ በአሁኑ ጊዜ የብአዴን ም/ሊቀመንበር ናቸው፡፡ ለነገሩ ዞር ብሎ ለተመለከተው ብአዴን በፓርቲ ደረጃ አስቀድሞ መተካካቱን መፈፀሙን መገንዘብ አያቅትም፡፡ ምክንያቱም በፓርቲው አመራርነት ከፍተኛውን የስልጣን እርከን የጨበጠው ግለሰብ በመንግስት ለከፍተኛ ሃላፊነት ስለሚመደብ፡፡

ብአዴን ይህን ሲፈፅም አቶ ገዱ በተለያዩ የሃላፊነት እርከኖች ያካበቱትን አቅምና ልምድ ታሳቢ ማድረጉ አይቀርም፡፡ አቶ አያሌው ጎበዜ ሰሞኑን ካደረጉት ቃለምልልስ መረዳት የሚቻለው ደግሞ እርሳቸው ለመተካት በተደጋጋሚ ጥያቄ ማቅረባቸው ተጨማሪ ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ ይሁንና ኪራይ ሰብሳቢውና ፅንፈኛው ሃይል የራሱን የተዛባ አመለካከት በሌላው ላይ ለመጫን ይመቸው ዘንድ መተካካቱ እየተፈፀመ ያለው በአዲሱ ትውልድ አመራሮች መካከል በመሆኑ ስኬታማ አይደለም በማለት ሂደቱን ለማጠልሸት ተረባርቧል፡፡ ይህ ግን ኢሕአዴግ አስቀድሞ በሰነዶቹ ባሰፈረው የመተካካት ስልትም ሆነ በነባራዊ ሁኔታው ሲታይ መሰረት የሌለው ነው፡፡

ለእንደዚህ አይነቱ የተቀነባበረ የሃሰት ዘመቻ ማጣፈጫ ተደርጎ በመቅረብ ላይ የሚገኘው ደግሞ ከፓርቲ የተገነጠለ የግል የፖለቲካ ስብዕና ለግለሰቦች ማላበስ ነው፡፡ ዘመቻው አንድ አመራር በተናጠል ያለው ህዝባዊ ሀገራዊ ፍቅር በአጠቃላዩ የብአዴን/ኢሕአዴግ አመራር ዘንድ ጥላቻ እንደሚያተርፍበትና ከስልጣን ለመነሳት እንደሚያበቃው እስከመግለፅም ይደርሳል፡፡

በመሰረቱ ብአዴን ከምስረታው ጀምሮ ካሉት መለያ ባህሪዎች ቀዳሚው ህዝባዊነቱ ነው፡፡ ምንግዜም ወገንተኝነቱ ለህዝብ የሆነና የእያንዳንዱ ውሳኔዎቹና ተግባሮቹ የመጨረሻ መለኪያ የሚያደርገውም የህዝብ ተጠቃሚነትን ነው፡፡ የአማራና ሌሎች በክልሉ ያሉ ብሄሮች የሚኖሩበት ሁኔታ እያስቆጨው ድህነትንና ኃላቀርነትን እየተፋለመ ያለ ነው፡፡ ይህ ባህሪ ፓርቲውን የሚመሩት ከፍተኛ አመራሮችና አባሎች ድምር እንጅ ‘ከላይ’ በፀጋ የታደለው አይደለም፡፡ ስለሆነም ማንም አመራርም ሆነ አባል ህዝባዊ ባህሪን መላበሱ ለፓርቲው እሴቶች ይበልጥ ተአማኒነቱን የሚያረጋግጥበት እንጅ በነዚህ ወገኖች እንደተባለው ጥርስ ውስጥ የሚያስገባው ሊሆን አይችልም፡፡

ጽንፈኛው ሃይሉ የአቶ አያሌው ጎበዜን ምግባር ከፓርቲው መርሆችና እምነቶች በተቃራኒ መሆኑን ለማሳየት በሚል የሚያቀርበው መረጃ ኢሕአዴግ ለሱዳን መንግስት መሬት ቆርሶ ሲሸጥ አቶ አያሌው ተቃውመዋል፤ አልፈርምም ብለዋል የሚል የበሬ ወለደ ቅጥፈት ነው፡፡ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት የፌዴራል መንግስትና የክልል መንግስታት የስልጣን ድንበር ስር የሚወድቁ ጉዳዮች ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 51 መሰረት ኢትዮጵያ ከማንኛውም ሌላ ሀገር ጋር በሚኖራት ግንኙነት የመደራደርና የመወሰን ስልጣን በፌዴራል መንግስቱ ስር የሚወድቅ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የሚደረግ ድንበርን ጨምሮ ማናቸውም ድርድር የፌዴራል መንግስት ሃላፊነት ነው፡፡ ድንበር ማካለል የፌደራል ስልጣን ነው ማለቴ ጉዳዩ ምን ያህል የወረደ የፈጠራ ወሬ መሆኑን ለማሳየት እንጅ ስልጣኑ የክልሉ መንግስት ቢሆን እንኳን መሬትን ለሌላ ሀገር አሳልፎ መስጠት የብአዴንም ሆነ ኢሕአዴግ መገለጫ አይደለም፡፡

የክልሉ ም/ቤት አስቸኳይ ጉባኤ መጥራቱንም ለፕሮፓጋንዳቸው ማጠናከሪያ ተጠቅመውበታል፡፡ በም/ቤቱም ሆነ በሌሎች አደረጃጀቶች አሰራር መሰረት አስቸኳይ ጉባዔ የሚጠራው የግድ አንድ ድንገተኛ ጉዳይ ሲያጋጥም ብቻ አይደለም፡፡ ለአብነት ም/ቤቶች ከቀጣዩ መደበኛ ጉባዔያቸው አስቀድሞ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ አጀንዳ ካለ ወይም በመደበኛ ጉባዔያቸው ወቅት ሊታዩ የሚገባቸው አጀንዳዎች ከበዙ ከወዲሁ ሌላ ጉባዔ ይጠራሉ፡፡ አንዳንድ አክሲዮን ማህበሮች አስቸኳይና መደበኛ ስብሰባቸውን በቀናት ልዩነት ማድረጋቸውም ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡ የአማራ ክልል ም/ቤትም ከአሁን በፊት ተደጋጋሚ አስቸኳይ ጉባዔዎችን አድርጓል፡፡

የም/ቤቱ መደበኛ ጉባኤ ባለፈው ጥቅምት ወር መካሄድ ሲገባው በተለያዩ ምክንያቶች ካለመካሄዱ ጋር በተገናኘ እስከ ቀጣዩ መደበኛ ጉባኤ ሊጠብቁ የማይችሉ ጉዳዮች በመኖራቸው አስቸኳይ ጉባኤው መጠራቱን አቶ አያሌው ጎበዜ ከዋልታ ጋር በነበራቸው ቆይታ አብራርተዋል፡፡ በክልሉ ከሰባት ያላነሱ የካቢኔ አባላት በተለያዩ ምክንያቶች ተጓድለው በተጠባባቂ ሲመሩ የነበረ በመሆኑ አስፈፃሚውን ሃይል

ማሟላት አስፈላጊ ነበር ብለዋል፡፡ በተመሳሳይ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተጓደሉ ዳኞችን ሹመት ማፅደቅም ጊዜ የሚሰጠው አልነበረም፡፡

በሌላ በኩል በቱርክ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር የነበሩት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ሆነው በመሰየማቸው በቱርክ ያለው ኤምባሲ ያለ አምባሳደር ቀይቷል፡፡ ከቱርክ ህዝብና መንግስት ጋር ያለን ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ የመጣ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በተለይ በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪው ዘርፍ የቱርክ ባለሀብቶች ተሳትፎ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነው፡፡ ባለፉት አስር አመታት ውስጥ 115 የቱርክ ባለሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት 1.2 ቢሊዮን ዶላር በሚያወጡ ፕሮጀክቶች ተሳትፈዋል፡፡ የሀገሪቱ የግንባታ ተቋራጮችም ወጪያቸው 2.4 ቢሊዮን ዶላር በሆኑ 21 ፕሮጀክቶች ላይ ተሳትፈዋል፡፡ ይህን ክፍት ቦታ በቶሎ በመሸፈን የሁለቱን ሀገሮች ግንኙነት ከዚህም በላይ ማሳደግ ይገባል፡፡ እንደውም መንግስት ለዚህ ታላቅ ሀገራዊ ሃላፊነት የመደባቸውን አምባሳደር በወቅቱ ለማዛወር የሚያስፈልገውን ዝግጅት ካላደረገ ነው በአሉታዊ ጎኑ ሊጠረጠርና ሊወቀስ የሚገባው፡፡

ፅንፈኛው የተቃውሞ ሃይል አሁን እየተከተለው ያለው ስልት ካሁን በፊትም ሲጠቀምበት የኖረ አካሄድ ነው፡፡ ኢሕአዴግ እንደ ግንባርና አባል ፓርቲዎቹም ከጥቂት ግለሰቦች ላይ የተንጠለጠሉ መሆናቸውን በተደጋጋሚ ሰብኮልናል፡፡ ጠብ ሲል ያየነው ነገር የለም እንጅ፡፡ በሌላ በኩል ፓርቲው ነባር አመራሮችን ከሃላፊነት አንስቶ በአዲስ ሃይል በተካ ቁጥር፤ ለተሻለ አፈፃፀም የምደባ ለውጥ ባደረገ ቁጥር፤ በአፈፃፀም አቅም ማነስ የማስተካከያ ርምጃ በወሰዱ ቁጥር ወይም በህግ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ነባር አመራሮችን ጭምር አሳልፎ በሰጠ ቁጥር የአዞ እንባቸውን ያነባሉ፡፡ ከዛን እለት በፊት አንድም ቀን እንኳን በበጎ አንስተውት የማያውቁትን አመራር ልዩ ፍጥረት አድርገው ያቀርቡልናል፡፡ መንገዱ ካሰቡት ግብ እንዳላደረሳቸው ሲረዱ ደግሞ ወደተለመደው የማጥላላት ዘመቻቸው ይገባሉ፡፡ በቅርቡ የተገለፀውም ይሄው ተፈጥሯዊ ባህሪያቸው ነው፡፡

አቶ አያሌው ጎበዜ ሰሞኑን ከመገናኛ ብዙሃን ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ አጀንዳው የብአዴንን አመራር በመከፋፈል ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ታስቦ የተቀረፀ መሆኑን በማጋለጣቸውና ይህንኑ የፀረ ሰላም ሃይሎችን ሴራ በመኮነናቸው ብቻ የአዞ እንባ ሲያፈስ የነበረው የፅንፈኛ ተቃዋሚው ካምፕ ተመልሶ የግለሰቡን ስብዕና በማጠልሸት ላይ ተጠምዷል፡፡

መስመሩ የተፋቸውን በማወደስና ‘የትግል’ አጋሩ በማድረግ የሚታወቀው ጽንፈኛ ተቃዋሚ የበሬ እንትን ይወድቅልኛል ብሎ ሲከተል እንደሚውለው ቀበሮ ብአዴን ያካሄደውን የመተካካት ሂደት ለሀሰት ፕሮፓጋንዳው ሊያውለው ቢሞክር የሚገርም አይሆንም፡፡ ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል እንዲሉ ተፈጥሯዊ ባህሪው ግድ የሚለው ስለሆነ ነው፡፡

በጥቅሉ ሲታይ ኪራይ ሰብሳቢዎች ስልጣንን የሚያዩት ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል በሚለው ልማዳው የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት ስለሆነ የአመራርን መተካካትን የሚመለከቱት በዚሁ የእይታ መነጽራቸው ነው፡፡ ስልጣንን የግል ጥቅምና ክብር ማካበቻ አድርገው ስለሚያዩት ማንም ሰው ይህንን ‘እድል’ አይኑ እያየ ሊለቅ አይችልም ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡ ከመሰረታዊ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባራቸው ተነስተው ሊደርሱ የሚችሉበት መደምደሚያም ይሄው ብቻ ስለሆነ ነው የአመራር መተካከቱን የሚያብጠለጥሉት፡፡